# ግልጽ ደብዳቤ

# ይድረስ ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የግንቦት 7 ሊቀመንበር

**አንክርዳድ እንክርድድ የተንከረደደ፤ ስንዴ መስሎ ገብቶ ስንቱን አሳበደ።**

ዶ/ር ብርሃኑ ሰሞኑን በድርጅትዎ ግንቦት 7 ውስጥ የተፈጠረውን አለመግባባት አስመልክተው ከአበሎችዎ ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት የሰጡትን አስተያየት ካንደበትዎ በመስማቴ እጅግ አዘንኩ ። ካለፉት ስህተቶቻቸው ተምረው ከዛሬ ነገ መደማመጥ ያቃተውን የተቃዋሚ ጎራ አስተባብረው ለአገራችን መድህን የሚሆን ግንባር በማደራጀቱ በኩል የበኩላቸውን ይወጣሉ ብለን ስንጠብቅ የራሴ የሚሉትን ድርጅት እንኳን አስማምተው መምራት ተስኖዎ ከጎንዎ የቆሙ ታጋይ ወንድሞችዎን በሚያሳፍር ሁኔታ ሲዘልፉ አደመጥኩ። የቅንጅት መፍረስ በተመለከተም "እኔ የለሁበትም ከደሙ ንጹህ ነኝ" በማለት በሌሎች ላይ ለመላከክ መድፈርዎ ስለከነከኝ የተሰማኝን ቅሬታ በአጭሩ ለማሳየት እንዲሁም ላንዳንድ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡና ለዉይይትም መነሻ ይሆን ዘንድ ሀሳቤን እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ።

**ስለ ቅንጅት መፍረስ**

ለቅንጅት መፍረስ በቀዳሚነት ተጠያቂዎቹ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልና አቶ ልደቱ አያሌው አንደሆኑ በማስመሰል ቀደም ሲል በይፋ ተንፍሰውት የማያውቁትን አቋምዎን ይፋዊ ባልሆነው የፓርቲያችሁ የውስጥ ስብሰባ ላይ ገልጠዋል ።ሀቅ ከእኔ ጋር ናት የሚሉ ከሆነ ይህን አቋምዎን ለምን ይፋ በሆነ መልኩ ለቅንጅት መስዋእት የከፈለው መላው ህዝብ እንዲያውቀው አላደረጉም? በእኔ እምነት ለቅንጅት መፍረስ ሁላችንም ሳናዉቀው የየበኩላችንን ብናበረክትም በግንባር ቀደምነት ተጠያቂ መሆን የሚገባዎ እርሰዎ እንጂ ኢንጅነር ሀይሉና ልደቱ ሊሆኑ አይችሉም።

በእርግጥ ኢንጅነር ሀይሉ ግትርና እልከኛ ናቸው።እኔ ያልኩት ካልሆነ ይላሉ።አንዳንድ ጊዜ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችን ያራምዳሉ ።ቅንጅትን አሰማምቶ የመምራት የአቅም ውሱንነት እንደነበረባቸውም ሁላችንም እናውቃለን።በሴረኝነት ተነሳስተው ቅንጅት እንዲፈርስ አድርገዋል የሚባለው ግን ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም እርስዎ ከዘመነኛ ባለስልጣናት ጋር በሶደሬና ላንጋኖ ውሰኪ ሲራጩ እርሳቸው የአድሜ መግፋትና የጤና መታወክ ሳያግዳቸው ታግለው ያታገሉና ለቅንጅት ምሰሶ የነበረውን መኢአድን ያፈሩ ናቸው፡

የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት /መአህድ/ለመፍረስና ለመበታተን ተቃርቦ በነበረበት ወቀት እርስዎና የቅርብ ጓደኞችዎ ድርጅቱን ከመሞት እንድታድኑት በአማላጅ ጭምር ተለምናችሁ "ፖለቲካ ውስጥ አንገባም" ብላችሁ አሻፈረኝ ስትሉ እርሳቸው የቀረበላቸውን ጥሪ ተቀብለው በቀውጢ ወቅት ትግሉን የተቀላቀሉ ናቸው። በሰሜን በደቡብ በምስራቅ በምእራብ ተንቀሰቀቅሰው ገንዘባቸዉን ፣እውቀታቸውንና ጊዜቸዉን በመሰዋት ለዴሞክራሲዊ ግንባታ ሂደት የበኩላቸውን አድርገዋል። በአንድ ወቅት ጎምጎፋ አርባ ምንጭ አካባቢ ከህዝብ ጋር ያደረጉትን ስብሰባና ውይይት አይቼ ምን ያህል ጠንክረው እንደሰሩ ለመገንዘብ ችያለሁ። ስለዚህ መኢአድን የመሰለ ለቅንጅትና ላጠቃላይ ትግሉ የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከተውን ድርጅት የፈጠሩ ሰው የድካማቸውና የትግላቸው ውጤት ለሆነው ቅንጅት መፍረስ ምክንየት ሊሆኑ የሚችሉበት ምክንያት ሊኖር አይችልም።

እኔና አርስዎ ለረጅም ጊዜ እንተዋወቃለን ፡፡ለጥቂት ጊዜም አብረን ሰርተናል። በአገራችን ጉዳዮች ላይም በየወቅቱ ሀሳቦችን ተለዋውጠናል።በተለይም ከቅንጅት ምስረታ በፊት በአንድ አጋጣሚ ተቃዋሚ ድርጅቶችን አስመልክተን ስንወያይ መላው ህዝብ የወያኔ ጭቆና እንዳንገፈገፈውና ለትግልና ለውጥ ዝግጁ መሆኑና በሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት መኢአድና ኢደፓ ድርጅታዊ መዋቅራቸውን እያጠናከሩና ሕዝባዊ መሰረታቸውን እየሰፉ መምጣታቸውን ገምግመናል። በሁለቱም ድርጅቶች አመራር ላይ የሚገኙት ግለሰቦች ግን ፖለቲካዊና የአመርር ብቃት የሌላቸው ኋላቀር አመለካከትና አስተሳሰብ ያላቸው በመሆኑ ትግሉን ከዚህ በኋላ መርተው የትም እንደማያደርሱትም ተማምነናል።ጊዜ ወስዶ ግለሰቦቹን በዘዴና በማግባባት ቀስ በቀስ በተማረና ብቃት ባለው የሰው ሀይል መለወጥ እንደሚገባ መነጋገራችንን አስታውሳለሁ።ይህንኑም በመጽሐፍዎ ጭምር አስቀምጠውታል።ይህንኑ የድርጅቶችን አመራር በሌላ የመተካት እቅድና ስልትዎን ከሌሎችም ጋር እንደተነጋገሩበት ስለማምን ይህን ጽሁፍ ያነበቡ ሁሉ አሰተያየታቸውን እንዲሰጡበት እጠይቃለሁ።

በእኔ እምነት እርስዎ ገና ቅንጅት ከመመስረቱ በፊት የተቃዋሚውን ትግል በተለይ በአገር ውስጥ በአገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙትን ድርጅቶች አመራሮች በስልት በመቀየር አጠቃላይ የተቃዋሚውን ትግል በበላይነት ለመምራት አቅደው ተንቀሳቅሰዋል።ህዝብ የሚወዳቸውንና የሚያከብራቸውን ተዋቂ ሰዎች በማግባባት ከፊት ለፊት እንዲቆሙልዎ በማድረግዎ ቅንጅት እንዲመሰረት አድርገዋል። በአቅድዎ መሰረት ቦታ የመንጠቁንና እርስ በርስ የማናከሱን ተግባርዎን ማከናዎን የጀመሩት ገና ለመቀናጀት ድርድር በሚካሄድበት ወቅት መሆኑን የገባን ዘግይቶ ነው።

ነባር አመራር አባላትን በማስወገድ አዲስ በሚቋቋመው ቅንጅት አመራር ውስጥ የወሳኝነት ቦታ ለመያዝ እንዲመችዎ በመኢአድና ኢደፓ መካከል ቀደም ሲል የነበረውን አለመግባባት በመጠቀም ኢንጅነር ሀይሉ “ልደቱ ከሚባል ወያኔ ጋር በጭራሽ አብሬ አልሰራም” ሲሉ “ጋሼ ሀይሉ ሁሉንም እናውቃለን ለጊዜው ግንባሩን እንመስርትና ለደቱን እናባርረዋለን” በማለት ያግባቡዋቸው እርስዎ እንደነበሩ አይስቱትም።

አቶ ልደቱም በበኩሉ “ሀይሉ ከሚባል ኋላቀርና አምባገነን ጋር አብሮ መስራት የማይሞከር ነው” ሲል ከልደቱ ጋር ቀደም ሲል የነበራችሁን የጠበቀ ወዳጅነት በመጠቀም “አሁን ግንባሩን እንመስርት ፣የሀይሉን ማንነት ሁላችንም የምናውቀው ስለሆነ ታገስ፣ በዘዴ እናስወግደዋለን “በማለት ምለው ተገዝተው እንዳግባቡትም ትዝ ይበልዎ።

ከልደቱ ጋር ድርና ማግ የነበራችሁ በመሆኑ በእቅዳችሁ መሰረት በቀዳሚነት መጠለፍና መውደቅ የነበረባቸው ኢንጅነሩ ነበሩ ፡፡ቀስበቀስ ሲታይ ግን ጠንካራ ድርጅትና ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ እንዳላቸው በመገንዘብዎ ወዳጅዎን ልደቱን ክደው ከኢንጅነሩ ጋር በመለጠፍ ለደቱን ጭዳ አደረጉት።ለዚህም አስቀድመው የቀርብ ወዳጆቹና ጓደኞቹ የነበሩትን ወጣቶች በማግባባትና በማሳሳት እንዲዘምቱበት አደረጉ። ቀደም ሲል ኢደፓ ውሰጥ የነበሩ ሽማግሌዎችን ለትግሉና ለአሰራር እንቅፋት በመሆናቸው ቀስ በቀስ ሊገለሉ እንደሚገባ ከልደቱ ጋር እንዳልዶለቱ ሁሉ እነርሱን ጭምር አስተባብረውና ድርጅታዊ ሥራ አካሂደው ለተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንትነት እንዳይበቃም አስደረጉት።

ልደቱ በተለይ ከእርስዎ ያልጠበቀው ክህደት የተፈጸመበት መሆኑ ስላንገበገበው ለቅንጅት ውህደት በአራቱም ድርጅቶች መሪዎች በተፈረመው የውህደት ሰነድ ላይ የኢደፓን ማህተም አላትምም አለ። በዚህ ሳቢያ ውህደቱ በወጉ ሳይቋጭ ቀረ። ድርጊቱም ለቅንጅት መበተን የላቀ አስተዋጽኦ አደረገ።ይህም የእርስዎ ሴራ ውጤት ነው ማለት ነው።

በዙዎቻችን ነባር አመራሮችን መቀየር የሚለው ቅስቀሳ ሌላ ድብቅ አጅንዳ ያዘለ መሆኑን የተገነዘብነው የቅንጅት አመራር ወህኒ ከወረደ በኋላ በተለይም እርሰዎ ብቻ በቀጥታ መመሪያና ትእዛዝ የሚሰጡት አካል በውስጥና በውጭ መቋቋሙን ስንሰማ ነው።

የቅንጅት አመራር ለወህኒ ከተዳረገ በኋላም ጥቂት ግለሰቦችን በአገር ውስጥና በውጭ አገር በማሰማራት በየደረጃው በአመራር ሀላፊነት ላይ ተመድበው በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉ የነበሩና የየወቅቱ እስራት አንግልትና ማሰፈራራት ሳይበግራቸው ለሰላማዊ ትግሉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ ነባር አባላትን በማግለል በሚስጥር በላያቸው ላይ ሌሎች አመራር ሰጭዎችና ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ አስደርገዋል። ይህን አፍራሽና ከፋፋይ እንቅስቃሴ ዘግይተውም ቢሆን የተገነዘቡ አባላት አድራጎቱን በመቃወምና በማጋለጥ በውጭም በውስጥም በመንቀሳቀሳቸው ለጊዜው ለማስቆም ቢሞከርም እርስዎ ቀድሞውኑ አስበውና አቅደው ያስጀመሩት ዘመቻ በመሆኑ ተከታዮችዎ እንዲገፉበት በማድረግዎ ድርጅቱ  ለሁለት ሰነጠቁት። በአለመግባባቱ ወቅት ሌሎች የቅርብ ወዳጆችዎና የስራ ባልደረቦችዎ ችግሮች በውይይትና በመነጋገር ይፈቱ ዘንድ በተደጋጋሚ ቢማጸኑዎትም አሻፈረኝ አሉ።የቅንጅትን መፍረስ የሚፈልጉት በመሆንዎ ራስዎን የድርጅት መርህ አስከባሪና ጠበቃ በማስመሰል ነገሮችን በማባባስ እርቅ እንዳይፈጠር ዋነኛ መሰናክል እንደነበሩም  በወቅቱ ችግሩን ለመፍታት ይጣጣሩ  የነበሩት ሁሉ ይመሰክራሉ።

ለመርህ ሲሉ ነው ። የተደበቀ አላማ አልነበራቸውም ተብሎ  እንኳን ቢገመት መከፋፈሉ ከተፈጠረ በኋላ የፈጸሟቸውን ቅንጅቱን በአጠቃላይ  የመናድ ተግባራት ጎልተው ስለሚታዩ ቅንጅትን በማፍረሱ ረገድ በቀዳሚነት ተጠያቂ ይሆናሉ።

ከኢንጅነር ሀይሉ ከተለያችሁ በኋላስ ለምን የማፍረሱን ሴራ ገፉበት?ከኢንጅነሩ ጋር መስራት ካልቻሉ ቀሪውን አካል አጠናክረው ለምን ወደ ትግሉ አልገቡም? ለምን ከወ/ሪት ብርቱካን ጋር በመሆን የቅንጅት ወራሽ የሆነ ጠንካራ ድርጅት ለመፍጠር አልፈለጉም?እነ ወ/ሪት ብርቱካን አንድነትን ለመፍጠርና በትግሉ ለመግፋት በቁርጠኝነት ተነሳስተው መንቀሳቀስ ሲጀምሩ እርሰዎና ተከታዮችዎ አሉባልታ በመንዛትና ነባር አባላትን በማደናገር እነርሱን ማደናቀፍን ለምን መረጣችሁ?

መልሱ አላማዎ የቅንጅትን ወራሽ መፍጠር ሳይሆን ከቅንጅት የተወሰነ አካል በመነጠል እርሰዎ የሚያዙበት የሚናገዙበት ድርጅት መፍጠር ነበረና አላማዎ እውን ሆነ። ቅንጅት ፈረሰ ።የራስዎን ግንቦት 7 መሰረቱ።

ከሁሉም በላይ የሚገርመው የማፍረሱ እንቅስቃሴ  በቅንጅት ላይ ብቻ አለመቆሙ ነው።አመራሩ እስር ላይ በነበረበት ወቅት ግለሰቦችን በውስጥም በውጭም አሰማርተው እንደነበር ከፍ ሲል ላስታውስዎ ሞክሬያለሁ። በነገራችን ላይ  አብዛኞቹ እንደራሴዎችዎ መደበኛ ሥራ ሰርተው የማያውቁ በመንግስታትና በግለሰቦች እርጥባን የሚተዳደሩ ነዳያን ቢጤ ለምን ሆኑ? ለዚህም ይመስለኛል የድርጅታችሁ ገንዘብና ንብረት ያለአግባብ በመባከኑ ከአባሎቻችሁ ጥያቄ የተነሰው።እነዚሁ እንደራሴዎች ቀደም ሲል በቅንጅት ስም ከተለያዩ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የመገናኘትና የመመካከር አጋጣሚዎችን አግኝተው ስለነበር ይህንኑ በመጠቀም በሌሎች ድርጅቶች ውስጥም በመስረግና አሉባልታዎችን በማናፈስ ነባር ድርጅቶች ሳይቀሩ የመከፋፈሉን ጽዋ እንዲቀምሱ አድርገዋል።

ዛሬ በጥምረት ስም ከግንቦት 7 ጋር እየሰራን ነው የሚሉት የኢህአፓ፣ የአርበኞች ግምባርና የኦነግ ስንጣቂዎች በሙሉ የእርስዎና መሰሎችዎ የማፍረስ ዘመቻ ውጤቶች መሆናቸውን የማናውቅ ይመስለዎታል?ይህ ጉዳይ እስከዛሬ ድረስ ሳይነካ የቆየ ቢሆንም ለወደፊቱ ግን የማፍረሱ ሴራ ተጎጅዎችም ሆኑ ስለጉዳዩ ተጨማሪ ማስረጃ ያላቸው ወገኖች አስተያየት እንዲሰጡበት አጋብዛለሁ።

**በእርሰዎ ላይ ስላደረው ትምክህት**

ከ97ቱ ምርጫ ውጤት በኋላ በተመራጭ ከንቲባነትዎ የአዲስ አበባ አስተዳደርን ለመረከብ ዝግጅት ያደርጉ በነበረበት ወቅት እንደርስዎ በህዝብ የተመረጡ ነገር ግን ዲግሪ አልባ ሆኑ ባልደረቦችዎን ትምክህት በተሞላበት ሁኔታ ሲያመናጭቋቸውና ሲየጣጥሏቸው አይቼ በወቅቱ ከሥራ ውጥረት ሳቢያ የመጣ ሊሆን ይችላል ብዬ ራሴን አጽናንቼው ነበር።ዛሬ ላይ ሳስበው ግን ቀድሞውኑ የተጠናዎትትዎት አባዜ ነበር።

ይህን ለማለት ያስደፈረኝ ሰሞኑን በተደረገ የውስጥ ስብሰባችሁ ወቅት በትግል ጓዶችዎ ላይ የሰነዘሩት አጸያፊ አሳፋሪ ዘለፋ ነው።"ከእነዚህ መሰሎች ጋር በመስራቴ ራሴ የቆሸሽኩ ሆኖ ነው የሚሰማኝ" እኮ ነው ያሉት።ይህ ከእርሰዎ የሚጠበቅ አልነበረም። በአንድ ወቅት ጠ/ሚኒስትር መለስ ፓርላማ ላይ ንግግር ሲደርጉ "የተጨመላለቀ አሰራር" የሚል አባባል ከአንደበታቸው አፈትልኮ በነበረበት ወቅት "የአገር መሪ ተብሎ እንዴት እነደዚህ ይናገራል?ለህዝብ ከበሬታ ስለሌለው ነው። የዱርዬ አነጋገር።የዱርዬ መንግስት" እንዳሏቸው አስታውሳለሁ።ታዲያ ምን ነከቶዎት ነው እርስዎን አምነው፣ በእርስዎ ተመክተው ፣የርስዎን የህይዎት መስዎእትነት ጭምር ሊያስከፍል የሚችለውን ሁለገብ የትግል ስልት ተቀብለው ፣እውቀት፣ ጊዜና ገንዘባቸውን ለትግሉ በማዋል ታግለው እያታገሉ ያሉትን ጓዶችዎን እንዲህ አዋርደውና አቃለው መሳቂያ መሳለቂያ የሚያደርጓቸው?በአድረጎትዎ አዝነንብዎታል።አፍረናልም።

በየመድረኩ ላይ ስለ ዴሞክራሲና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብትና ነጻነት ሲናገሩ በእውነትም ከልብዎ መስሎን ነበር።እነዚህ አባሎችዎ መርህ ይከበር፣ የጋራ አመራር ይኑረን ፣የዘመድ አዝማድ አሰራር እየተንሰራፋ ነው፣ የድርጅቱ ገንዘብ ያለ አግባብ እየባከነ ስለሆነ ችግሮቻችን ተባብሰው ለትግሉ እንቅፋት እንዳይሆኑ በግልጽነት በዴሞክራሲያዊ መንገድ በጋራ ተወያይተን መፍትሄ እንፈልግለት ከማለት ውጭ የእርሰዎን ስልጣንና ቦታ አልተመኙ ምን አደረጉ ብለው ነው ያን ያህል መዓት ያወረዱባቸው? በራሳችሁ ድርጅት ውሰጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ካላወቃችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ  ከየት ልታመጡለት ነው? ከውጭ መንግስታት በእርዳታ?

የዘለፋውና የማንአህሎኝነቱ  መነሻው የጓዶችዎ ጥፋት ሳይሆን በላይዎ ላይ ያደረው የእኔ ብቻ ያልኩት ካልሆነ አምባገነናዊ አባዜ ነው።ዛሬ የተቃዋሚ መሪ ሆነው በሀሳብ የሚለዩዎትንና የሚቃወሙዎትን ሁሉ የሚዘልፉና የሚያዋርዱ ከሆነ  ነገ የመንግሰት ሥልጣን ቢጨብጡማ ቅሬታ ያሰማውን ሁሉ እንደ ጎመን ሊከትፉት ነው ማለት ነው።እግዚአብሄር ይጠብቀን።

እርስዎ የድርጅታችሁን አባላት ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት በመጋፋት በስድብና ማሸማቀቅ ላይ ተሰማርተዋል። የእርሰዎ ተከታዮች ደግሞ በሰለጠነው አገር በአሜሪካ የሚኖሩ ወገኖቻችንን የመደራጀትና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ እንዲሁም የፈለጉትን የመደገፍና የመቃወም መብት በመጋፋት ጸረ ዴሞክራሲ የሆነ የወሮበላ ተግባራትን ሲያከናወኑ መሰንበታቸውን በሰሞኑ በተለያዩ ድረ ገፆች ላይ አሰተውያለሁ።

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ፌደሬሽን የእርስዎ ድርጅት መሪ ካድሬዎች በሆኑ ግለሰቦች ቀስቃሽነትና አሰተባባሪነት እንደ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ለሁለት የመሰንጠቅ እድል ያጋጠመው መሆኑን ከሰማን ሰንብተናል። ሰሞኑን ሁለቱም ቡድኖች በአሜሪካ የተለያዩ ሁለት ከተሞች የስፖርት ውድድሮችን እንዳዘጋጁም ሰማን።ይህን መሰል መከፋፈል መፈጠሩ በእውነቱ አሳዛኝ ነው።ኢትጵያውያን አንድ ፌደሬሽን ብቻ እንደቀድሞው ቢኖረን ምንኛ መልካም ነበር ።እንዳለመታደል ሆኖ መከፋፈሉ አይቀሬ ከሆነና መስማማት ካልቻሉ ደግሞ ሁለቱም ቡድኖች ደጋፊና ተከታይ እስካገኙ ድረስ በፈለጉት መንገድ የመጓዝ መብታቸው መታወቅ አለበት።

የእርስዎ ተከታዮች "እኛን የምትደግፍ ዳላስ ላይ እንገናኝ "ከማለት ይልቅ የሌላውን ወገን ደጋፊ መብት በሚጋፋ መልኩ በጋዜጣ በራዲዮ፣ በተሽከርካሪ በመዘዋወር ፣ወረቀት በመበተን ፣ግለሰቦችን በማሰፈራራት እንዲሁም አድማ በማስመታት ጭምር ግለሰቦችን ለማግለል ሰጣጣሩ መክረማቸውን ታላቅ ጀበዱ አንደተሰራ ሁሉ ዜናውን በድምጽም በምስልም አየነው። ሰማነው። ዴሞክራሲ በሰፈነባት አገረ አሜሪካ ሰውን በጡንቻ ለማሳመን የምትጣጣሩ ከሆነ እዚህ አዲስ አበባ ስልጣን ይዛችሁ ቢሆን ኖሮ ምን ይውጠን ነበር?ታዲያ እናንተ ከወያኔ በምን ትሻላላችሁ? በምንም አትሻሉም።እንዲያውም የባሳችሁ ትሆናላችሁ ብየ እሰጋለሁ።

ዶ/ር ብርሃኑ! ወደ ፖለቲካው አለም ከገቡ ጀምሮ በየወቅቱ የትግል ስልት፣ የአስተሳሰብ ፣የአመለካከትና የአቋም ለውጦችን በወቅቱ ሲቀያይሩ ይስተዋላል።ታዲያ አሁን የያዙትን የሁለገብ ትግል ስልት ነገ ጠዋት ምክንያቶችን በመደርደር እነደማይለዉጡት ምን ማስተማመኛ አለ?ምንም የለም።

ዛሬ ላቀረባኋቸው ጥያቄዎችና ለሰነዘርኳቸው አሰተያቶች ተገቢ መልስ እንደሚሰጡኝ በማመን በቀጣይ ቀሪ ጥያቄዎችን ይገፍ አስከምቀርብ ቸር ይግጠመን።

ተማም አባገሮ temamabagero@yahoo.com

አዲስ አበባ